# በእችክችክ የግጥም መድብል ላይ የተደረገ የይዘት ትንተና

በ
ወለላ እጄቻ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሁፍ ትምህርት
ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
ሰኔ 2001 ዓ.ም

# ማውጫ

1.መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2 የጥናቱ አላማ ........ 2

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 2

1.4 የጥናቱ ወሰን ........ 2

1.5 የጥናቱ ዘዴ ........ 2

2. ክለሳ ድርሳን

2.1 ትወራዊ መሰረት ........ 3

2.1.1 የስነ ግጥም ምንነት ........ 3

2.1.2 የስነ ግጥም ይዘት ትንተና ........ 4

2.2 የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ........ 4

3. በ"እችክችክ" የግጥም መፅሀፍ ውስጥ በተካተቱ ግጥሞች የይዘት ትንተና

3.1 ማህበራዊ ጉዳዮች ........ 6

3.1.1 ፍቅር ........ 6

3.1.2 ስለ እኩይ ባህርያት የሚያወሱ ........ 10

3.1.3 ስለ ሰናይ ባህርያት የሚያወሩ ........ 15

3.2 ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ግጥሞች ........ 17

3.3 ሀገራዊ ጉዳዮችን የሚቃኙ ........ 21

3.4 ሌላ ........ 22

ማጠቃለያ ........ 24

ዋቢ መፃሕፍት ........ 25

ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው ........ 26

# ምስጋና

በቅድሚያ ለዚህ ላበቃኝ አምላክ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡ በማስከተልም ጥናቱ የተሳካ እንዲሆን ተጀምሮ እስኪያበቃ ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሰይሉ እርማትና ጠቃሚ ምክራቸውን በመለገስ ከጎኔ ላልተለዩት አማካሪዬ ለአቶ የወንድወሰን አውላቸው ልባዊ ምስጋነዬን አቀርባለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አዚህ እንድደርስ የዘወትር ድጋፋቸው ላልተለየኝ ቤተሰቦቼ እንዲሁም ያላሰለሰ የሞራልና የገንዘብ እገዛ በማድረግ ለተንከባከበኝ ጓደኛዬ ፍቅረ በረቀዐ ላቅ ያለ ምስጋናን ሳልለግስ አላልፍም፡፡ በመጨረሻም መፅሀፉን በመተየብና በማረም ያለመታከት ላገዘችኝ ሰብለ ባንትይርጉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

## ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ሥነ - ጽሁፍ ገሀዱን አለም መሠረት አድርጎ የሚሰናዳ ሲሆን የማህበረሰቡን ህይወት መፈተሻና መግለጫ መንገድ ነው፡፡ ስነግጥም ከስነፅሁፍ ዘርፎች አንዱ ነውና ሌሎች የስነፅሁፍ ዘርፎች ለማህበረሰቡ የሚያበረክቱትን ፋይዳ ግጥምም ይጋራል፡፡

እንዲያውም ከስነፅሁፍ ዘርፎች አንጋፋ እንደመሆኑ ከሰው ልጅ ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው፡፡ ዘሪሁን (1998፣73) "ስነግጥም በእጅጉ ጥንታዊነት እንዳለው የሚነገርለት የኪነጥበብ ዘር ነው፡፡ የሰው ልጆች ለብዙ ዘመናት ደስታና ሀዘናቸውን ምኞት ፍላጎታቸውን የአኗኗር ሁኔታቸውንና ልዩልዩ ገጠመኞቻቸውን በማንጎራጎርና በማዜም ሲገልፁበት ኖረዋል፡፡"

ስለዚህ ስነግጥምን መመርመር ማለት የየዘመኑን ማህበረሰብ ልዩልዩ የህይወት ገጠመኞች ማጤን ይሆናል፡፡ ግጥሞችን ተወዳጅ የሚያደርጋቸውም ከቅርፃቸው ባሻገር ያለው ትውልድን የማሳየት ብቃታቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ለዛ ባለው መንገድ ሀሳብንና ስሜትን ለማቅረብ ያስችላል፡፡አሜሪካን አካዳሚ ኢንሳይክሎፒዲያ(1986፣15) ‹‹ የግጥም ቃል ልዩ ትርጉም ያለው ሲሆን መዝገበቃላት ውስጥ ካለው ትርጉም ነፃ የሆነና ከመደበኛው ቋንቋ ያፈነገጠ ነው፡፡››ይላል ያፈነገጠ ነገርን መመርመር ያስደስታልና በዚህም ነው በ2000 ዓ.ም ታትሞ በወጣው የአቶ አብርሃም ረታ እችክችክ መፅሀፍ ውስጥ በተካተቱ ግጥሞች ጥናት ለማድረግ የታለመው፡፡

አቶ አብርሃም ረታ ዓለሙ በይርጋለም ከተማ ከቤተሰቦቹ ጋር በኖረባቸው ከ1980ዎቹ በፊት በመምህርነት ሞያ ከተማዋን ሲያገለግል የቆየ ሲሆን በ1990 ዓ.ም በመገናኛ ብዙሃን ማሰልጠኛ ተቋም በጋዜጠኝነት ሠልጥኗል ፡፡ እንዲሁም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ "እርስዎ ለእርስዎ" እምድር ላይ ይሰራ ነበር ፡፡ ምንም እንኳ ይህ ደራሲና ገጣሚ በአሁኑ ወቅት ከዚህ አለም በሞት የተለየ ቢሆንም ከላይ በተጠቀሰው አምድ ላይ ሲሰራ ለሚነሱ ጥያቄዎች አዝናኝ መልስ በመስጠት ይታወቅ ነበር፡፡

ይህ ደራሲና ገጣሚ በጥራዝ መልክ አኑሮ ያለፋቸው መፃህፍት "አከራይ-ተከራይ-አካከራይ" ፡በአከራይና ተከራይ ህይወት ዙሪያ የሚያጠነጥን ፡"አልንተባልን አስባልን" "አባባ ሰው የለውም" ፡ የዶር አብርሃም ፈለቀ የግጥም ስብስቦች "የያዘው ቢላዋ እና ብእር" ና ለዚህ ጥናት የተመረጠው እችክችክ የግጥም መፅሀፍ ነው ፡፡

በእችክችክ መፅሃፍ ላይ ትኩረት እንዲሰጥ ተፅእኖ ያደረገው "አንቺ እናት ፤ለሞኜ" በሚል ርዕስ የተገጠመው ግጥም ነው ፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ገጣሚው ለእናቱ ያለውን ፍቅር አውርቶ የማይጠግብና እንደውም ሟች እናቱን ለማስታወስ ከሞቱባቸው ቀን ጀምሮ ያነደዳቸው ሻማዎች ከአመታት በኋላ በአንድ ትልቅ ትሪ ላይ ቢያንስ ግማሽ ሜትር ከፍታ መስራቱን ይነገራል፡፡ እናም በግጥሙ ይህንን የጠነከረ ፍቅር የምትሸረሽርን ሴት በማመስጠር የገለፀባት መንገድ ስለሚያስደምም ነው፡፡ የዚህ ግጥም ይዘት የፈቀደውን ባሻው ሰዓት እየለገሰች ነፍስያውን በሀሴት የምትሞላለትን ሴት የሚያሞካሽበትና በተቃራኒው ከእናትም በላይ በላቀው ፍቅሯ ከአብራኳ የተካፈላትን እንዲዘነጋት በማድረጓ ግን ጠላቱ እንጂ ወዳጁ ብቻ እንዳልሆነች ይገልፃል፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የግጥም መፅሀፍ የቃላት ሀብታምነትና ብቃት፣የሀሳቦቹ ጥልቅነትና ጥቅልነት ለመተንተን የተዘጋጁ በመምሰላቸው የግጥም መፅሀፉን ምርጥና ምጥቅ አሰኝተውታል፡፡ ስለሆነም እንደዚህ ዓይነት ፅሁፍን መተንተን አንድም ትፍስህትን ያመነጫል፡፡ አንድም ደግሞ የግጥሙን ሀሳብ በማፍታታት መልዕክቱን በቀላሉ ወደ አንባቢ አይንና ጆሮ ለማድረስ ያስችላል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ በእችክችክ የግጥም መድብል ላይ የቀረቡ ግጥሞች ላይ የይዘት ትንተና በማድረግ በግጥሞቹ የተዳሰሱ አበይት ጉዳዮችን ማሳየት ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህ ጥናት ጠቀሜታ በመፅሀፍ ላይ ጥናት ሲደረግ የመጀመሪያው እንደመሆኑ መጠን ከዚህ በኂላ ጥናት ለማድረግ ለሚሹ ሁሉ እንደመነሻነት ያገለግላል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአቶ አብርሃም ረታ በተገጠመውና በ2000 ዓ.ም ታትሞ በወጣው እችክችክ የግጥም መፅሀፍ ውስጥ በሚገኙ ግጥሞች ላይ የይዘት ትንተና ብቻ ማድረግ ፡፡

## 1.5 የጥናቱ ዘዴ

ጥናታዊ ፅሁፍ ቀዳማይ ተግባሩ የመፅሀፉን ግጥሞች በጥልቀት ማንበብና ከይዘታቸው አንፃር መፈረጅ ነው፡፡ ለትንተናውም ከየፈርጁ ይበልጥ የሚወክሉ ግጥሞች በመምረጥ ተወስደው ገላጭ ዘዴን በመጠቀም ትንተና ተካሂዶባቸዋል ፡፡

ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳን

### 2.1 ትወራዊ መሰረት

#### 2.1.1 የስነ ግጥም ምንነት

ስነ ግጥም በጣም ረጅም እድሜ ያለውና የሰው ልጅ ማህበራዊ ኑሮን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ለመግባቢያነት ሲጠቀምበት እንደኖረ የተለያዩ መረጃዎች ያትታሉ፡፡ መነሻውን ማህበራዊ ገጠመኝ ማድረጉና አንጋፋ መሆኑም አንድ ወጥ ብያኔ እንዳይገኝለት አድርገዋል፡፡ አንድ ወጥ ብየና መስጠት ማስቸገሩን ዘሪሁን አስፋው (1998፤73) ሲገልፁ “ስነግጥም በኪነጥበብ ዘመንታሪክ ብዙ የኖረ ለመሆኑ እንደየዘመኑ ፍልስፍና እንደየዘመኑ ገናን የኪነጥበብ ፈለግ እንደየገጣሚውና እንደየስነፅሁፍ አዋቂው አተያይና የኪነጥበብ ዝንባሌ የተለያዩ ብያኔዎች ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡” ይላል፡፡

ምንም እንኳ ስነግጥም አንድ ወጥ ብያኔ መስጠት አዳጋች ቢሆንም የዕለትተዕለት ነባራዊ ዓለምን ዕውነታ ለምናብ አግዝፎ ለማቅረብ የሚያስችል የፈጠራ ጥበብ መሆኑን ግን መናገር ይቻላል፡፡ ሰፊ ሀሳብን ቁጥብ በሆነና ስሜትን በሚነኩ ቃላት የመግለፅ ኃይሉ ከሌሎች የጥበብ ዘርፎች እንደሚለየውም እንዲሁ፡፡

ብርሃኑ ገበየሁ የአማርኛ ስነግጥም በሚለው መፅሀፍ የተለያዩ ምሁራን ስለ ግጥም ምንነት ያሉትን ካቀረቡት አንዱ ሳሙኤል ጆንሰን የተናገረው ነው፡፡ ይህም ‹‹ ስነ-ግጥም ምንድንነው?፡፡›› ተብሎ ሲጠየቅ ‹‹ አዬ ጌታው ስነ-ግጥም እንዲህ ነው ከማለት ይልቅ ያልሆነውን (ነገር) መናገር እጅግ ቀላል ነው፡፡ ሁላችንም ብርሃን ምን እነደሆነ እናውቃለን ነገርግን ስለብርሃን ምንነት ለመግለፅና ለማብራራት እንቸገራለን፡፡›› ብለዋል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ለስነግጥም ወጥ ብያኔ ያልተገኘለት ገሚሱ በራሱ አተያይና ገጠመኝ እንዲህ ነው ስለሚለው፣ሌላው ታላላቅ ስሜቶች የሚዘከርበት መሆኑን ስለሚያንፀባርቅ የተቀረው ከሰው ልጅ የዕለትተዕለት ትግል ጋር ስለሚያቆራኘው አንዳንዱ ደግሞ ጥልቀት ያለውን ሀሳብ ማቅረቢያ ነው የሚል ፅሳቤን ስለሚያቀርብ ነው፡፡ በአጠቃላይ ስነግጥም የሚሰጠው ብያኔ የሚገለፀው የስነፅሁፍ አዋቂው ከዕይታ መጠኑ እና ለእርሱ ከሚመስለው ነገር ተነስቶ ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡

## 2.1.2 የስነ-ግጥም ይዘት ትንተና

የይዘት ትንተና በርካታ ርዕስ ጉዳዮችን በመዳሰስ በውስጣቸው የሚገኙትን ሀሳቦች፣መልዕክቶችና ስሜቶች ለመገንዘብ የሚያስችል ዘዴ ነው። የይዘት ትንተናን ምንነት በተመለከተ የስነ አእምሮ መዝገበ ቃላትን ጠቅሶ ደረጀ ገብሬ እንዲህ አስቀምጦታል፡፡

የይዘት ትንተና የተለያዩ ጭብጦች የያዙ ሰነዶች መልዕክቶችና ሀሳቦችና አስተያየቶችን የሚተነተኑባቸው የተለያዩ ዘዴዎችን የሚያቅፍ ነው፡፡ እንዲህ ያለ ትንተና በአብዛኛው የተወሰኑ ቃላት፣ሀረጋት፣ግብ መች የሀሳብ መግለጫዎች የመሳሰሉት በሰነድ ውስጥ ስንት ጊዜ እየተደጋገሙ እንደሚመጡ ለማወቅ የሚያስችል ላቅ ያለ ስልታዊ ዘዴዎችን ሁሉይይዛል፡፡ ረቦር (1985፣152)

ትንተና የታመቁ ሀሳቦችን በማፍታታት በሀሳብ ውስብስብነት የተፈጠረ ብዥታን ያጠራል ፡፡ ስለዚህም አንድን የፅሁፍን ሥራ ደጋግመን ካነበብን በኃላ ያለውን ረብ ገላልዖ ማሳያ መሣሪያ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የስነግጥም ይዘት ትንተናም ገጣሚው በህይወት ገጠመኞቹ ከቃረማቸው ተሞክሮዎች በመነሳት ለተደራሲያኑ ማስተላለፍ የወደዳቸውን ቁምነገሮች በተንታኙ ዓይን ማቅረቢያ መንገድ ነው፡፡ እንዲሁም በግጥም ቃላት አማካኝነት የሚተላለፈውን መልዕክት በማፍታታት ማቅረቢያ ስልትም ነው፡፡

“የግጥም ትንተና ግጥሞችን ከቅርፅ ከይዘትና ከታሪክ አኳያ የመፈተሻ ሂደት ሲሆን ዓላማውም የራስንና የሌሎችን አረዳድና ለስራው የተሰጠውን አድናቆት ያካትታል፡፡” http…www./ate/

በአጠቃላይ የአንድን ግጥም ይዘት ይህ ነው ለማለት አስቀድሞ ግጥሙን በጥልቀት ማንበብና መፈተሽ ተገቢ ነው ፡፡ ምክንያቱም አንድን ግጥም በአንዴ ንባብ ይዘቱን በትክክል ለመረዳት ስለሚያዳግት ነው፡፡ ጠልቆ ለማንበብ የገጣሚውን ስሜት ለመረዳትና ጥሩ ትንተና ለማድረግ ያስችላል፡፡ ትንተናውም ተነባቢነት እንዲኖረው ያግዛል፤ አንባቢን ማስደሰት ያስችላል፡፡ “የግጥም ትርጉም ስሜትን፣አመለካከትንና አስተሳሰብን ያካትታል፡፡የግጥም ትርጉም ጠቀሜታ የአንባቢን ስሜት መንካት መቻል ነው፡፡” (Burton፣1979፣129)፡፡

## 2.2 የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል የቀረቡ፣በግጥም ይዘት ላይ ትንተና ያደረጉ ስራዎች አሉ፡፡ እነዚህ ዲማፆች በአብዛኛው በቃላዊ ግጥሞችና በጋዜጣዎች ለይ በወጡ ግጥሞች ለይዘትና ቅርፅ እይታ ትኩረት የሰጡ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ

በመፅሀፍ ታትሞ በወጡ ግጥሞች የይዘት ትንተና  አፅንዖት እንደመስጠቱ መጠን ተዛማጅ የተደረጉት በመፅሀፍ ላይ ከተሠሩ ጥናቶች ብቻ ናቸው፡፡

ጥናቶቹ በተፃፉበት ዓመት ቅደም ተከተል ስንመለከት መጀመሪያ “በአፈር ያነሳ ስጋ” የግጥም መፅሀፍ ውስጥ ባሉ ግጥሞች ሂሳዊ ትንተና (ንጉሴ፤1973) የተደረገበት ጥናት ነው፡፡በዚህ ጥናት ውስጥ ንጉሴ ስለጭብጥ ምንነት ከገለፀ በኋላ ግጥሞቹ የህብረተሰቡን የኑሮ መልክ የሚያሳዩ ፣የተፈጥሮን ሂደት የሚያንፀባርቁ ፣በኑሮ ገጠመኝ ላይ የሚያተኩሩ ስለሰው ልጅ የህይወት ትርጉም ጥያቄ የሚያቀርቡ በማለት ከፋፍሎ ትንተና አድርጎባቸዋል ፡፡ እንዲሁም ስለ ምት ስለ ዘይቤና ቃላት አጠቃቀም አሳይተዋል፡፡

ሌላው የመዘክር ክፍሎም ‹‹ አቤ ጉበኛው›› ( 1974 ) ግጥም መፅሀፍ የተጠናበት ሥራ ነው፡፡ ይህ ጥናት በቀደምትነት በሀገራችን ስለሚሰራባቸው የግጥም ዓይነቶች እንደ አብነት እየጠቀሰ አሳይቷል፡፡ቅርፅን አስመልክቶም ገጣሚው የተጠቀመባቸውን የግጥም ዓይነቶች ፣አሠኛኘት፣ቤት አመታት ፣ዘይቤያዊ አነጋገሮች የቃላት አጠቃቀምና የአፃፃፍ ስልት አሳይቷል፡፡ በመተንተንም ጭምር አመልክቷል፡፡ በይዘቱ ስር ስለሀገራችን እድገት ተፈጥሮ ፣ስለፍቅር ሀይማኖትን የሚመለከቱ መልዕክቶች የሰው ልጅ የተለያዩ ክስተቶች ቅኔያዊ መልክ ያላቸው ብሎ በመከፋፈል የይዘታቸውን ተንትኗል ግጥሞቹ ቀስቃሽ መካሪና አዝናኝ መሆናቸውን ገልጿል፡፡

እንዲሁም የግርማ ገብሬ ሁለት በታተሙ የአቶ አያልነህ ሙላቱ የግጥም መፅሀፎች የይዘትና የቅርፅ ትንተና (1986) የሚል ነው፡፡ በዚህ ዲማፅ የግጥሞቹን ቅድመእና ድህረ ስልሳስድስት ተብለው በመመደብ የይዘት ትንተና ተደርጐባቸዋል ፡፡ በእነዚህ ታሪካዊ ወቅቶችም የተፈፀሙትን ማህበራዊ ፣ኢኮኖሚያዊእና ፖለቲካዊ አመለካከቶች የታዩባቸው መሆናቸው ተገልጿል፡፡ እንዲሁም የአገጣጠም ስልት የተቃኘበት ሲሆን አሰኛኘት ፣የቃላት ምርጫና የዘይቤ አጠቃቀም ተጐሏል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተመለከቱት ፅሁፎች አፅንኦት የተሰጡባቸው ጉዳዮች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ይኸውም የተለያዩ ገጣሚያንን ስራዎች ፖለቲካዊና ማህበራዊ ብሎ በመመደብ የይዘት ትንተና ፣የቅርፅ፣አሰኛኘት ፣ቤት አመታትና የቃላት ምርጫን ተመልክተዋል፡፡ ይህ ጥናትም ከቀረቡት መመረቂያ ፅሁፎች ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በእችክእችክ መፅሀፍ ላይ በመስራቱና በይዘት ትንተና ላይ ብቻ ትኩረት በማድረጉ ከተጠቀሱት ዲማፆች ይለየዋል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

### 3. በ‹‹እችክችክ›› የግጥም መፅሀፍ ውስጥ በተካተቱ ግጥሞች የይዘት ትንተና

#### 3.1 ማህበራዊ ጉዳዮች

በዚህ ክፍል በ2000ዓ.ም ታትሞ በወጣው የአብርሃም ረታ የግጥም መፅሀፍ ውስጥ በተካተቱ ግጥሞች የይዘት ትንተና ተደርጎል፡፡ በመፅሀፉ ውስጥ ከሚገኝ ግጥሞች ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚያነሱ ሲሆኑ በመቀጠል ፖለቲካዊና ሀገራዊ ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡

በጥናቱ 18 ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚያነሱ ግጥሞች ታይተዋል በዚህም ስለፍቅር ፣ስለኑሮ/ህይወት/፣ስለእኩይና ሠናይባህርያት፣ስለአጉልልማድና ሌሎችም ሲነሱ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚያወሱት ደግሞ 9 ናቸው፡፡ በዚህ ስር እንደንዑስ የታዩት ምርጫ 97፣ስለነፃነት፣ዲሞክራሲ ናቸው፡፡ የሀገር ውበትና ጀግንነትም እንዲሁ በሀገራዊ ጉዳዮች ስር የተተነተኑ ናቸው፡፡

##### 3.1.1 ፍቅር

በዚህ ስር የምንመለከታቸው የፆታዊና ወላጆችን ፍቅር የሚቃኙ ግጥሞችን ነው፡፡ በቅድሚያ ለማየት የተሞከረው (ብቅ ያለ ሰው የለ ፣35)

በግጥሙ እንደነፍሱ የሚወዳት ግን የተለየችው ፍቅረኛው ከዛሬ ነገ ትመጣለች በሚል መንፈስ የሚጠብቅ ሰው ይታያል፡፡

ይኸው ዞሮ መጣ ሰኔ ተመለሰ
መንገድ መንገዱ ላይ ዕንቤ እየፈሰሰ

ዱካዋ ባለመገኘቷ እንባዉ እንደጅረት እየወረደ ቢጠብቃት ብቅ አለማለቷ እንዳስደነገጠው ይገልፃል፡፡

እንደጥቅምት ቁር - አጥንት የምትመታ
እንደሐምሌ ነሓሴ ብርዷ የሚያሰቅቅ
ልቤስ አልቆረጠም
አለ እየጠበቀ
አለ እየታገለ፡፡

(ብቅ ያለ ሰው የለ፣35)

ፍቅሯ ውስጣዊ ነፍሱን ሲያንዘፈዝፈው እርሷ ግን ከመዳፉ ባትገኝም ‹‹ላም አለ በሰማይ›› እንዲሉ እሱም በዳጉሰ ተስፋ እየጠበቃት መሆኑን ይናገራል፡፡

በአጠቃላይ መለየት ምን ያህል እንደሚጉዳና ሰቀቀንን በሰው ላይ ዘርቶ እንደሚያሳቅቅ በማሳየት የፍቅርን ሀያልነት ያስረግጣል፡፡

ሌላው በአንዲት ሴት ፍቅር የቀለጠን ሰው ያመለክታል፡፡

ምነው ቀን ባልነበር
ምነው ሌት ባልነበር
መምሸትም ባልነበር
መንጋትም ባልነበር
ሁልጊዜእኔ'ናንቺ
ተቃቅፈን እንድንኖር

ይህ ሰው ለሔዋኑ ባለው የጐነ ፍቅር ከጐኑ ባትርቅ፣የሚለያያቸው አንድም ነገር ባይኖር ሀሴት እንደሚሰማው ይገልፃል፡፡

በጠረንሽ አጥነው
በከናፈር ሽገንዘው
በወዝሽ ከፍነው (ፍቅርና ሞት፣54)

በእቅፏ ጥላስር ሆኖ ፣‹‹ዋልያ ወደምንጭ ውሃ ይናፍቅ ዘንድ ›› እንዲል ታላቁ መፅሀፍ ቅዱስ፣እሱም ከናፍሯን፣ወዟን ልቧንና ጡቷን እንደሚሻ ያመለክታል፡፡ እንዲሁም ከሁለመናዋ አጐዳኝታው ፣በፍቅሯ ባጅተው ዝንተ አለም ከእርሷ ጋር የሚኖርበትን ሁኔታ ቢያመቻቹለት እንደእንቦሳ ጥጃ እንደሚያዘልለው ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ ማንም ሰው ያፈቀረውን ሲያጣ አውላላ ሜዳ ላይ እንደቀረ ይሰማዋል፡፡ በመሆኑም መቼም ቢሆን ከፍቅሩ ባይለይ እንደሚመርጥ ለመመልከት ያስችላል፡፡

ቀጥሎ‹‹ሔዋን›› የሚለው ግጥም ሴት ልጅ የትኛውንም መንገድ ተጠቅማ ወንድን በቁጥጥር ስር ማድረግ እንደምትችል ይጠቁማል፡፡

ባይንሽ ባካሄድሽ በሴታዊነት ብልሃት፣
ንገሪው ጥቀሽው በይ ተሽኰርመሚበት፣
ሔዋን ፍንጭ ሰጥታው ጥቅሻና ምልክት
አዳም መቼም ቢሆን አልታየም ሲያመልጣት፡፡

የምን ዕባብ ... በለስ
ምን ማፈር መቅለስለስ
የምን ዓቤል ቃዬል
ምን ገሃነም ሲያል
ጥቀሽው ይጥቀስሽ
አውድቂው ያውድቅሽ
አንቺ ከጅለሽው ማንም አያመልጥሽ!

(ሔዋን፣52)

አንቺ በመማረክ ጉዳይ የክህነትን ካባ ደርበሻልና በፍቅር ፈልገሽው ማንም ከመዳፍሽ እንዳይወጣ አውቃለሁ ይላል፡፡ ጌታ አዳምን በገነት ሲያኖረው ከአንዷ በለስ ውጭ ሁሉንም በገነት ውስጥ ያሉትን ዛፎች እንዲበላ ፈቅዶለት ነበር፤ነገር ግን ሔዋን በእባብ ለይ ባደረ ዲያብሎስ ስትገዛ መረታቱን ለብቻዋ ይዛ አልተቀመጠችም፡፡ ለአጋሯ አዳም የበላችውን የሀጥያት ዕፅ ስታቋድሰው ጥቂት ቢያቅማማም ለሀሳቧ መንበርከኩን ግን አማራጭ የሌለው አማራጭ አድርጎት ነበር፡፡ እንደገናም ቃዬልና አቤል ሲወለዱ ሁለቱም ሴት መንትያ ነበሯቸው፡፡ የአቤል መንታ አስቀያሚ የቃዬል መንታ ደግሞ ውብ ነበረች፡፡ ነገርግን እናትና አባታቸው ዘር እንዲቀጥል በማሰብ የቃዬልን መንታ ለአቤል ፣የአቤልን ደግሞ ለቃዬል እንደ ሚስት ሰጧቸው፡፡ ነገር ግን ለቃዬል የደረሰችው አስቀያሚዋ በመሆኗ ከልቡ አዘነ፤ከፍተኛ የቅናት መንፈስንም ፀነሰ፡፡ ይህም ወንድሙን ወደመግደል መንደርደሪያ ሆኖታል፡፡ ከላይ ያሉት መፅሀፍቅዱሳዊ ታሪኮች የሚያመለክቱን ወንድ ልጅ ለሴት ሲል ማንኛውንም እኩይ ድርጊት እንደሚፈፅም ያሳያሉ፡፡ በግጥሙም የተገለፀው ይኸው ነው፡፡

ቀጥሎ በሚቀርበው ግጥም እሱ በሚገባ ያልኖረበትን ዘመን ወላጆቹ በመታተር ያሳለፉና አሁን ግን በሞት ስለተለዩት እናትና አባቱ የሚያወሳ ሰው ተስሏል፡፡

በህልም ይማከሯል፣በህልም ይጣገቧል

በእስር ቤትም ቢሆን አይዞህ አለሁ ይላል፡፡

ይህ ሰው እናትና አባቱ በህይወት በኖሩበት ዘመን ብሎም ከሞቱ በኋላ የታሰረበት ወህኒ ቤት ውስጥ በህልሙ እየተገለጡ እንደሚጐበኙትና እንደሚያበረታቱት ይገለፃል፡፡

መች አነሰኝና ዛሬ በሃያ አመት
እንደገና ብቅ አልሽ?
እስሩን መረታት፣መታመሙን መዳን
መታረዙን መልበስ፤
አድርጎ ለማሰብ፣የወላጅ ትዝታ
እንዲህ ብርታት ሲሰጥ፤
አይዞህ ሚል ከሆነ-ሞተ ማለት ከንቱ
መኖር ምን ረብ አለው?
አባብዬ አልሞትክም
እማምዬ አልሞትሽም
(እናትና አባት፣72)

አባትና እናቱ በምድር ሳሉ ለእርሱ ህይወት ማማር ሲወጡና ሲወርዱ የኖረበት ዘመን ሲያስደስተው እንደሚኖር ይገልፃል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በህልሙ እየተገለጡ ሲያነጋግሩት በዕውን ያገኛቸው ያህል ሀሴት እንደሚሰማውም ያክላል፡፡ በመሆኑም ከሃያ አመት በፊት የሞቱ ሰዎች በህልም እየመጡ የሚያበረታቱ ከሆነ ወላጆጄ አልሞቱም

ይልቁንስ የሞትኩት እኔ አይን አይገባ ስራ ሳልፈፅም የኖርኩት እንጂ በማለት በህይወት ዘመኑ ከወላጆቹ የተሻለ ተግባር ያለመፈፀሙም የቆጨው ይመስላል፡፡ በአጠቃላይ ግጥሙ ወላጆች ለልጆቻቸው ያላቸውን የማይነጥፍ ፍቅር ሞትም እንኳ ቢሆን የማይቀለብሰው እንዲሁም ምክርና ተግሳፃቸው ህይወትን እንደሚዘራ ያጠይቃል፡፡ ብሎም የዘመኑ ትውልድ ወላጆች ያለፉባቸውን የትጋት ህይወት መድገም ወይም መሞከር እንደተሳነው ይጠቁማል፡፡

ቀጣዩ ግጥም በዘመኑ የሚታየውን የሸንገላ  ፍቅር ያሳያል፡፡

ሰው ከባህር ዓሳዎች

ምንድን

ምን ይማራል

ከሰማይ ወፎችስ ምን ሐቅ ያስተውላል

ከቀፎ ንቦችስ

ምን ዕውቀት ይማራል?!

እንስሳት እንኳን ያላቸውን መቻቻል ፣መግባባትናፍቅር የዘመኑ ሰው ሊላበስ አለመቻሉ ያስደንቃል፡፡

የኛ ዜጐችማ ዘመዶች ወገኖች

እየተቋሰሉ

እየተደለሉ

መኖር ጌጥ ሆነና

ነፍስሽ ነፍሴ

ሕይወትሽ ሕይወቴ

እየተባባሉ

ይደላለላሉ

ይሸናገላሉ

ይህ ትውልድ እውነተኛ ፍቅር መጐናፀፍ ተስኖታል፤እንጥፍጣፊ ፍቅር ሳይኖረው አንዱ ሌላውን ፣ሌላው አንዱን ከልብ ያፈቅረ ለመምሰል መጣጣርና ቅጥፈት የነገሰበትን የፍቅር ህይወት መምራት ሰው መርሁ ሆኗል፡፡

ኡፈፍፍ፡ ወሸከሬዎች

ውሸታሞችሁሉ

እንዴት ይሰለቻሉ!? (የሚሰለች ነገር፣22)

ታዲያም በከንቱ ውዳሴ የታጀበ ፍቅር ይጎፈንናል:: ስለሆነም ይህ እኩይምግባር በማህበረሰቡ ውስጥ ማቆጥቆጥ እንደሌለበትና ተመንግሎ እንዲወጣ ይገልፃል፡፡

3.1.2 ስለ እኩይ በህሪያት የሚያወሱ

በዚህ ርዕስ ስር የሚመለለከቱት ግጥሞች ያልታገሉበትን ጥቅም መሻት ፣ክፋትና እኔ ብቻ አዋቂ ነኝ ባይነት ፣ቅናት ፣ጥልቅባይነትና ከበራን መሻት ያሳያሉ፡፡

በቀደምትነት የተተነተነው ግጥም‹‹ አፌላይትፋብኝ›› የሚለው ግጥም ሲሆን ይህ ግጥም ስለ ጥቅማጥቅም ሁለነገሩ ላይ እንደፈቀዳቸው እንዲፎልሉበት ራሱን አሳልፎ የሰጠና ስለነፃነቱ ቅንጣት ታህል ደንታ የሌለው ይልቅዬን ለጊዜው ፈንጠዝያ የነከሩት ቦታ የሚዘፍቅ ሰውን ያመለክታል::

ስለመስት ግዴታ ጠልቆ ቢገባኝም
ስለህላፊነትና ተጠያቂነት ጠንቅቄ ብረዳም
ስመኝ የኖርኩትን ፣ስራብ የከረምኩትን
ሳልም የባጀሁትን
ሥልጣን አስታቀፈኝ

‹‹መብት›› ‹‹ግዴታ›› የሚሉ ቃላት ለእኔ ከቃለትነታቸው በዘለለ ምንም ስሜት አይሰጡኝም፡፡ በዚህች ምድር ለይ ለእኔ ትልቁ ቁምነገር ስልጣን ማግኘት ነው፡፡የተንደላቀቀ ህይወት የሚመሩ ሰዎች ዓይነት ኑሮ ከተቸረኝ ፣የመሻቶቼ ሁሉ ጥም ከተቀረጠልኝ ወሰኑ ያልተገደበ ደስታ ይኖረኛል፡፡ ከዚህ በኋላ እንደመዳዳታቸው ከእግራቸው ስር አጋድመው የእግራቸውን ትቢያ ቢያስልሱኝ ምናምንት ቅሬታ አይሰማኝም፡

የምን ዲሞክራሲ-የምን እኩልነት
ባፍንጫዬ ይውጣ የቃላት ስርርቶ
(አፌላይ ትፋብኝ፣8)

ዲሞክራሲም መብቴ ይከበር ብዬም አልከራከርም እንደውም ዲሞከራሲ እኮ ቃላት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት ቃል እንጂ ሌላ ምንም አይደለም በማለት ይናገራል፡፡በአጠቃላይ የሚደረግበት በደል ከአእምሮው በላይ ሆኖ እንደእሬትቢጎመዝዘውም እንኳ ያሻው ይፈፀምለት እንጂ ለህሊናው ሳይጨነቅ መሬት ልሶ የሚኖር ለከርስስ
እንጂ ለህሊናስ የማይኖርን ግለሰብ ያሄሳል፡፡

ቀጣዩ ግጥም በወዳጁ ላይ ገደብ የለሽ ቅናት የተጣባውን ሰው ያሳየናል፡፡
እንደማያልፍ የለም -ሁሉም ነገር አልፏል
ልፊታ- ተዳርሷል፡፡
ግንባርክን ሳነበው ወሬህን ስሰማ
ገርሞኛል -ደንቆኛል
በለመደ ዐመልህ
የበለጥኩህ መስሎህ
መታሰር ሀብት ሆኖ… ትቀናብኛለህ፡፡
ኧረ ይህም ሲያንሰው
ገድለውልኝ ባረፍኩ
ሆነ አሉ ስዕለትህ፡፡

ይህ ወሰን ያጣ ቅናት የተንፀባረቀው ይበልጠኛል ብሎ ባሰበውና በእስር ለይ ባለ ሰው መሆኑን ይገልፃል፡፡ ይህ ሰው በጓደኛው ላይ የሚያነባቸው አሉታዊ የአካል ገፅታዎች እንዳሳዘኑት ይናገራል፡፡ የቅናቱ የክፋቱ ክፋት በጓደኛው እስራት እንኳ ሳይቀር እንዲመቀኝ ስታጋፍጠው ዝም ብሎ መቀበሉ አስደንቆታል፡፡ መታሰር ጥሪት እነዳልሆነና የእርሱ መሞት ለምን ደስታ ሊሰጠው እንደቻለ አስገርታል፡፡ ምናልባት ሁለቱም አፈር ናቸውና ምስጥ ሆኖ ሊበላው እንደማይችልም ያሳያል፡፡ ስለሆነም እንዲህ በቅናት ጆንያ መጠቅለሉ ጠቀሜታ እንደሌለውና በደረሰበት የምቀኝነት ውርጅብኝ ልቡ የተሰበረ ሰው መሆኑን ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ ግጥሙ ቅናት ማህበረሰቡን የሚጎዳ ነቀርሳ በመሆኑ እንዲወገድ ለማሄስ ሞክሯል፡፡

በማስከተል ‹‹ቢንቢ›› የሚለው ግጥም ውስጥ ‹‹ቢንቢ›› ውክል የተደረገው ህይወቱን በሙሉ በሰው ላይ ክፋትን በማድረግ ስመጥር ለሆነ ሰው ነው፡፡

ባወቅሁት ታሪክህ
በቀደመው ዝናህ
እጅግ ስለምፈራህ
ባጉበር ውስጥ ሆኜ
ነው የምወዳጅህ፡፡
(ቢንቢ-51)

ይህ ሰው የሰርክ ተግባሩ ተንኮልን ማድረጉ ስለሚታወቅ የርኩሰት ስራው እንዳይነካን ጓደኛ ማድረግ ካለብን በከፍተኛ ጥንቃቄ ተሞልተን መሆን እንዳለበት ይገልፃል፡፡ በአጠቃላይ ግጥሙ የሰውን ህይወት ለማበላሸት የመይቦዝኑ ሰዎቸወን በብልሃት መከታተል እንዳለብን ያሳስበናል፡፡

ሌለው ግጥም አንዳችም በሌላቸው ተሰጥኦ ራሳቸውን ከደራሲያን ከተዋንያን ፣ከገጣምያንና ከሌሎች ሁሉ ጉራ በመመደብ እኔ ልታይበት የሚያዘወትሩ ሰዎችን ያመለክታል፡፡

መህበር ተከልለው
ሙያ ተጠልለው
ስለሚተካቸው ትውልድ
የሚትከነከኑ፡

ከእነርሱም አብልጦ የሚሰራ ተተኪ ምቾታቸውን ይነሳቸዋል፡፡ በባዶአቸው አቅም አድምተው ከሚሰሩና ጥበባቸው ሰዎችን ከሚማርክ ባለሙያዎች ጋር ራሳቸውን መፈረጅ ምንም ረብ እንደማይሰጣቸው ይገልፃል፡፡

አሸም በሉን ሲሉ
አንቱ በሉን ሲሉ
እንሸላለም ሲሉ
ገረሙኝ እነሱ፡፡

(አሻምበሉን፣67)

ራሳቸውን ሰማይ ጥግ በመድረስ ሌሎች በሚሰጧቸው ከበራና ቁልምጫ ርካታን ለመሸመት ይሯሯጣሉ፡፡ ትኩረት ቢነፈጉም እንደምንም ተፍጨርጭረው ራሳቸውን ለመስወደስ ይሻሉ በማለት ይወርፏቸዋል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ሰዎች ይህን መጥፎ ምግባራቸውን እንዲያርሙ መካሪና ገሳፂ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለማለት ‹‹ታጣወይ ጠፋወይ- እነ.እነአንቱዬን ‹ሃይ ባይ?›› በሚለው ስንኝ ሀሳቡን ያጠነክራል፡፡ በአጠቃላይ በየትኛውም ስፍራ አንቱታ ሻዬችን በሌባሻይ መርህ አድኖ ባህሪያቸውን ማቅረብ እንደሚገባ ለማጠየቅ ሽቷል፡፡

በማስከተል ‹‹ወንጀል-ወንጌል›› የሚለው ግጥም የሚያወራው የሰውን ልጅ እየበደለ ግን መንፈሳዊ ስራን በመፈፀም በደሉን ለመፋቅ የሚጥር ሰውን ያመለክታል፡፡

በደልህን ለማጠብ ጭንቅህን ለማራገፍ
የተፈቀደ ነው ከጆሮ ላይ ቆርጠህ
በየአፉ መወተፍ፡፡

ይህን ግለሰብ የንፁሃንን ላብ እየቀማህና ምስኪኖችን እያስጨነቅህ ካካበትከው ሀብት የአይን ጉድፍ የምታህለዋን እየቆነጠርክ ቤተክርስቲያን ወይም መስኪድ ማሣነፅ አግባብ አይደለም፡፡ የምትሰራውን መንፈሳዊ ሥራ ለበደልህ ማስተሰሪያ አይሆንም፡፡ ስለሆነም ደሀዎችን አትበድል ፡፡ በአጠቃላይ ወንጀልን ሰርቶ የፃድቃንን በሚመስል ሥራ ለማካካስ መታገል ምንም ቱርፋት እንደሌለው አስረግጧል፡፡

ሌላው ግጥም አንባቢን በሚያማልል መልኩ ግጥምን የማይፅፍ ሰዎች በተሻለ መጠን መፃፍ አክል መጫጫራቸውንና አንባቢን ማደናገራቸውን መቅጨት ይናገራል፡፡

እና ግጥምም በአዲስ መልክ
ጀምረናል-ብንልስ?
...ግጥም የሻጭ ገዥ፣የሸማች የሸቃጭ
ሸቀጥ አሻንጉሊት ሁና በአዲስ መልክ
አንባቢን ከጠራች
በወራት ሸለቆ፣ ስንኝ በመቀየር
ቃላት በመወልወል
ቀለም በመቀባት...
ከተብሰከሰከች፤

ተመራጭ በሚመስል ግን ምንም ቅያሬ በሌለው መንገድ በመፃፍ ፣አዲስ ስልት የተከተሉ በማስመሰል፣የአንባቢን ስሜትለመቆንጠጥ መሯሯጡ ተገቢ እንዳልሆነም ያሳስባል፡፡ ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ቃላትን በመኳኳልና በማበጃጀት ብቻ ግጥም ተፅፎ የሚቀርብ ከሆነ የቀረው እንደሚሻልም ያመለክታል፡፡ ማንም ሰው እየተነሳ የፈቀደውን ሥራ አየር ባየር የሚያጧጥፍበት ዘመን ቢሆንም ማንም ፀሃፊ መሳይ ከመሬት ተነስቶ ግጥምን መፃፍ ተገቢ አይደለም፡፡ ጥሩ አንባቢም እኮ ከጥሩ ደራሲ አይተናነስም እናም በሚገባቸው ባለሙያዎች የተፃፉትን ግጥሞች ብናነብ እኛም ገጣሚ ነን፡፡

ከጩኸት ይልቅ ፀጥታ ስለሚሻል
ምናለ ካቃተው ፣ቢተወው ዝም ቢል!
(ግጥም በአዲስ መልክ፣32.33)

ስለዚህ ጥሩ አንባቢ መሆን ካልቻልን ካላዋቂ ሳሚነት የቀረው ይሻለናልና አርፈን እንቀመጥ በማለት ይገሥፃቸዋል፡፡ በአጠቃላይ በዘመኑ እንደአሸን እየፈሉካሉት የግጥም መድብሎች አብዛኞቹ ደረጃቸውን ያልጠበቁ መሆናቸው አሳሳቢ እንደሆነ ለመጠቆም ሽቷል፡፡

ቀጣዩ ግጥም ለጥበብ ሥራ መበልፀግ ያለሰለሰ ጥረት የሚያደርጉት ታላላቆች እንዳይሞካሹ ስራዎቻቸውን የሚሸፍኑባቸው ሰዎች አግባብነት የሌለው ተግባር እየፈፀሙ እንደሆነ ይወቅሳቸዋል፡፡

ስለአንድ ወገን ብቻ ደጋግመን በመዝፈን
ሠርክ በማፋደስ፣ዞትር በማጋነን
ሌላው የሚረሳ የሚሸፈን መስሎን

አንዳንድ የጥበብ ሰዎች የሌሎች ታላቅነት ልቆ እንዳይታይ እንጥራለን፡፡ በግልም ሆነ በቡድን እየተደራጀን የአንድ ወገን ብቻ የጥበብ ውጤት እንዲታይ በአንድነት ድምፃችንን ከፍ አድርገን እንዘምራለን፡፡ በማለት ትችቱን ያስቀምጣል፡፡

ለሁሉም ለመጥቀም
ሁሉንም ለመሸለም
ቢሰጠን መቶ ዕድል
እነዴት አንዷን ዕለት፣አንዷን መድረክ እንኳ
ያንዲቷን ቀን በዓል
ለሌላኛው አቻው
ማድረግ ያቅተናል?!

ደጋፊዎች የሌሉት ሰው አማላይ ስራ ቢያቀርብም ተቀበቀይነቱ አናሳ ነው፡፡ ምርጥ የጥበብ ሰው እያለ ደጋፊው እንሁን እነጂ አሰስገሰስ ሥራ ያቀረበውን እናሞካሻለን፡፡

በሚቹ ትከሻ ክንፍ ክንፍ በማብቀል
ቋሚው ተስፋቆርጦ ራሱን እንዲገድል
ካራ በማቀበል
በማግለል ማስገለል
ጥበብን መነጠል
ጠቢባንን መግደል
መኰትኰት ቂም በቀል
ጥላቻን መፈልፈል
… ቢቀርብን ምናል፡፡

በተለይ የሞቱ ሰዎችን ብቻ በማንቆለጳጰስ በህይወት ያሉ ጠቢባንን ስሜታቸው እንዲጎዳ የማያቋርጥ ትግል ማድረግ ቢቀርብን ምናለ? የትኛውም የጥበብ ሰው ታዲያ ለመመስገን በሎ መሞት አለበት ወይ? በማለት ጥያቄያዊ ሀሳቡን ይሠነዝራል፡፡

ስለመረጥኩ እንጂ በቀልን መታገል
ማግለልን ማስገለል
ያንጎልን በመንጉል በመዘክዘክ ፈንታ
……. ትቼውም ዝም ብል
ለጊዜው ነው እንጂ፣ አይቻልም ከቶ፣
በዚህ ዓይነት መንገድ ጠቢባንን ለመግደል…
(ዋርካና ጠቢቡ፣102.103)

ምጡቅ የጥበብ ስራ የሠራና የሚሠሩ ዋናዎቻችን ለምን አይታሰቡም የሚል የሚል መንፈስ ተጣብቶኝ እንጂ እኔ  ዝም ብል እንኳ መቼም መችም የኪነትን ሥራ ማጥፋት እንዳይቻል ሊታወቅ ይገባል በማለት ያስረግጣል፡፡ በአጠቃላይ ጥበብ ታላቅ እምርታ እንድታሳይ ይህ ነው የማይባል ድርሻ ያበረከቱትን ለአብነትም አፍወርቅ ተክሌ መወደስ እንዳለባቸው አበክሮ ያዘክራል፡፡

ቀጣዩ ግጥም ‹‹ እንቅልፌ የውሃጥም›› የሚለው ሲሆን እንቅልፍን የስንፍና ተምሳሌት በመድረግ ለዕድገትና ብልፅግና የማይጣጣርን ሰው ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡

ቤት የለኝም እኔ አልጋም የለኝ እኔ
በፀሀይ ጨረቃ ግድ የለኝም እኔ
ታሪክና ተረት ለምኔ ለምኔ
ሕልሜ ነፃነቴ አገሬ ወገኔ
እንቅልፌ ናት ለኔ፡ፅድቄና ኩነኔ

በድህነት ገመድ የተተበተብኩ ብሆንም ስለብልፅግና ጠፈር ላይ ስለማደር፣ስለጥንካሬ ና ብርታት ቢተረክልኝ አይገደኝም፡፡ ስንፍናዬን ሽቻለሁና እርሷን በጀርባዬ አዝዬ መኖር ይሻለኛል፡፡ ‹‹ ፅድቅና ኩነኔ›› ሲል ከባነንኩኝ የተሻለ ነገር ማስገኛዬ ካልተጋሁኝ መጥፊያዬ ናት ለማለት የፈለገ ይመስላል፡፡

የመተኛት ርግብ የመንቃት አሞራ
በግፍ በጭካኔ በምቀኝ ነውና
እንቅልፌን አደራ፡

ድካም ሰላሟ፣ጠንክሮ መስራት ግን ጠላቷ የሆነችው አለመትጋቴ የምትወገደው በጥሮግሮ  ስለሆነ ስለጥንካሬ መስማት አልፈልግም፡፡

ይህቻትልህና አንከበከብህልኝ…
በየጢሻው ገስጋሽ፣በየፈፋው ደናሽ፣
በየጉባው አልቃሽ፣በየመልካው ቀዳሽ፣
አድርግልኝና…

‹‹በየጢሻው ገስጋሽ››፣አጣብቂኝ ህይወት ገፊ፣ ‹‹በየፈፋው ደናሽ ›› በዝቅተኛ ኑሮ የምረካ ፣‹‹ በየጉባኤው አልቃሽ›› ፣ስለበታችነት አላዛኝ  ‹‹በየመልካው ቀዳሽ›› ፣ስለወረደ

ህይወት ዘማሪ መሆን ፈላጊ ነኝ በማለት ይገልፃል፡፡ የሰፋ ድህነትን እስክጋፈጥ ስንፍናዬ ከእኔ ጋር እንደተዋደደች ትኑር፡፡ የትም የትም ዛሬ ‹‹ባህር›› ሲል የዝቅተኝነት እረመጥ የለብልበኝ ለማለት አስቧል፡፡

እንቅልፌን በማጣት
እስከ እድሜ ልኬ
ባኪም በአረቂ ስታገም እንዳልኖር
ጠብቀኝ አምላኬ፡፡
(እንቅልፌ የውነጥም፣31)

ስለሆነም ከስንፍናዬ አላቃቂ ‹‹ሀኪም›› ፣መካሪ ‹‹አረቄ›› የቆፍጣንነት /የጥንካሬ ህይወት/ እንዳይጎበኙኝ ይሁን በማለት ይናገራል፡፡ በአጠቃላይ አለመፍጨርጨርን ገንዘብ ያደረጉ ደካማ ሰዎችን በተለይ በሀገራችን ላይ አጥልቶ ያለውን ያልዳበረ የሥራ ባህል በምፀት ለማሄስ ሽቷል፡፡

3.1.3 ስለ ሠናይ ባህሪያት የሚያወሩ

በዚህ ርዕስ ስር አስቀድሞ ለመተንተን የታሰበው ‹‹ምንዛሬና ውለድ›› የሚለው ግጥም ሲሆን ለመወሳት የተወደደው መልካም ስራን መስራት በእንቅል የሚገኝ ቱሩፋት እንዳለው ነው፡፡

የተኙቶ መንቃት አግባርና አውጋር
ባውሊያዋ በኩል እንደምትጠቁመው
በአልጋ ምቾት አይደል ዕንቅልፍ ምትገኘው፡፡
ከመጋደምህ በፊት
በሰራኸው መጥፎ ፣ወይም ደግ ልክ ነው፡፡
አንተ በጐ ነገር ለሌች አባድር
ዕንቅልፍህ ወለዱን፣መንዘወራ እስመንዝራ
ዓይንህ ውስጥ ትጨምር
ትራስህ ስር ታኖር
ታኖር ታኖርና
ባህሩን በመርከብ
ጠፈሩን በአየር
ይዛህ ጭልጥ ነው፡፡
(ምንዛሬና ወለድ፣56)

በሰላም የተንቆጠቆጠች እንቅልፍ ማግኘት ታለቅ ፀጋና በርካቶች የሚናፍቁት ቢሆንም እርሷን ለማግኘት ከመኝታችን በፊት በምንተገብራቸው መልካም ምግባራት እንደሆነ ይናገራል፡፡ ‹‹በሰፈሩት ቁና›› እንዲሆን ሁሌም የቀና ሥራ ውጤት ደስታ ክፋት ሥራ ውጤት ጭንቀት መሆኑ አሌ አይባልምና ይህንን እውንታ ልንጋፈጥ ግድ ፡፡ በአጠቃላይ የምንሰራቸው በጎ ነገሮች ለህሊናችን ፍፁማዊ መረጋጋት ያለስቡለታልና እንረካለን ይህም ታለቅ ትርፍ ነው በማለት ማህበረሰቡ ለመልካም ስራ እንዲነሳሳ ያበረታታል፡፡

በቀጣዩ ግጥም አንደም ሰሃ የሌለበት ፍፁማዊ ሰው ተብሎ ይገኛል፡፡

ጋዜጤኞች ቢጠይቁት
ቢቆፍሩት ፣ቢቆፍሩት፤
መልስ እማያልቅበት-ይህ አስገራሚ ፍጥረት
ደራሲዎች ቢፅፉላት ቢፅፉላት…
አላልቅም ያላቸው የሉ ተዓምራት፤

ይህ ሰው ሁለነገሩ የሚማርክና አንዳችም የሚጣል ነገር የሌለው ያሰበው የተሳካለት ፣ሂድ ያለው የሚሄድለት ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለውና እልፍ አእላፍት ወትልፊት አስደናቂ ታሪኮችን ያስመዘገበ ነው፡፡ ታዲያ ይህ የክፍለዘመኑ ምርጥ ዓለሙ ሁሉ ቢሆን መሻቱን ሲገልፅ

እኔም አንተም አንቺም
ሁላችን ብንሆንስ? በማለት ጥያቄ አዘል
(አስገራሚው ሰውዬ Egoist፣65)

ሀሳቡን ይሰነዝራል፡፡ በአጠቃላይ በዚህች ምድር ላይ ያሉ ሰዎች አስተሳሰብ መለያየትን ያልተቀበለና ጨዋ ባሌጌ፣ ክፉ ደግ፣ ትንሽ ትልቅ … የሚሉ ቃላትን መስማት ያንገፈገፈው ይመስላል፡፡ ስለሆነም በዚህች ዓለም ስንኖር የሁላችንንም የሁሌም በእኩል መጠን ስኬታማነት ናፍቋል፡፡

3.1.4 ስለኑሮ /ህይወት/ የሚያወሱ …

በዚህ ዓብይ ርዕስ ስር የመጀመሪያው ግጥም « የአቡክያ ድምፅ» ነው፡፡ በዚህ ግጥም አቡኪያ በአንዷት ገጠር ተወልዶ ህይወቱን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ አኗኗር ዘይቤ ያሳለፈ ግለሰብ ውኩል ነው፡፡

ሎሚ ስንወረውር
ስንጫወት ስንጨፍር

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በተለያዩ በዓላት በተለይ በመስቀል የተቃራኒ ፆታን እይታ ለማግኘት የሚደረገው ግብግብ ጠንካራ እንደሆነና ይህ ሰውም በዛላይ ተሳታፊ እንደነበር ያወሳል፡፡ በዚህ ጨዋታ ላይ ከአንዷት ሴት ጋር በፍቅር እንደተቆራኙና አስራ ሁለት ልጆች እንደወለዱም ያጠይቃሉ፡፡ ልጆቻቸውም ልጆች ወለዱና የልጅ ልጅ ለማየት በቁ ለማለት

የልጅ ልጆች አየን
እስከ አያት ቅማያት ድረስ ዘለቅን

ይህን ሁሉ አይቼው ሰማንያ ዓመት ሲሞላው መንፈሳዊ ስራን መስራት እንዳዘወተረ ይናገራል፡፡

ዕድሜዬ ሰማንያ በደራሰ ጊዜ
ገራገራውን መቃኘት
የታመመ መጠየቅ
የተጣላ ማስጣስታረቅ
ክብረ በዓላትን ማድመቅ
የዕለት ተዕለት ጉዳዬ ሆነ

በእንዲህ ያሉ ሁኔታ ዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሞላኝ፣መቶ አመት እንደምደፍን እየነገሩኝም ጮቤ አስረገጡኝ፡፡ ዘጠና ዘጠኝ አመት ሞልቶኝ ግን ለልመና ሳልወጣ የእኝየ ልጆች ግን ለልመና ተሰማሩ፡፡ ይህ አልባሌ ተግባራቸውን ከምመለከት ግን መሞት ይሻለኛል፡፡ ምክንያቱም ባደረግሁላቸው ነገር ተጠቃሚ ሳይሆኑ ፣ልመናቸው ካልቀረ ምንም አልፈይድምና መቶ ዓመት መድፈኑ ምን ረብ አለው፡፡

ላያመሰግኑ
ታክመው ላይድኑ
ካልጨመርኩኝ ምንም
ምን ያደርጋል ታዲያ
መቶ አመት መድፈኑ፡፡
(የአቡክያ ድምፅ፣40)

በአጠቃላይ አባቶች በሰሩላቸው ብቻ ልባቸውን አንሰራፍተውና ሀሳባቸውን ጥለው አልባሌ ኑሮአቸውን በአባቶቻቸው ሀብት ላይ የተከሉ ይህም አልሳካ ሲላቸው መናኛ

ዘዴዎችን በመጠቀም ገንዘብ የሚቃርሙትና ውዳቂ ህይወት የሚመሩ ትውልዶችን ያሔሳል፡፡ የድሮ አባቶችም በአሁኑ ትውልድ ያለመርካት እነንደሚታይባቸው ያመለክታል፡፡

በመቀጠል ‹‹በጊዜ ለኩሉ›› የሚለው ግጥም ሲሆን ሁሉንም ነገር በአርምሞ ብንከታተል እያንዳንዷ ጉዳይ የምትሳካበት ጊዜ እንዳለው ያጠይቃል፡፡

ትዕግስት ላደላቸው በ'ጊዜ ለኩሉ
ሥርየት ይከተላል፣
ርጋታ ያገመው ቁስልም ይጠግጋል፣
የታሰረ ቢሆን-ይዘገያል እንጂ
ቆይቶ ይፈታል፣
ያጣም ዕድሜ ሲያገኝ ባለፀጋ ይሆናል፣
በሽተኛም ለምዶት ከህመሙ ይስማማል፣
ፍትሕ የጐደለው በትርዕ ይካሳል፣
(በጊዜ ለኩሉ፣106)

‹‹ለሁሉም ጊዜ አለው›› እንዲል መፅሀፉ መክብብ በችግርና ስቃይ፣በረሀብና ስቃይ ቢታለፍ ፣ትዕግስት ካለ ሁሉም በጊዜው ይከናወን ዘንድ ግድ ነው፡፡ በግጥሙ አስረግጦ ለመንገር የታሰበው ያሰቡት ነገር ባሰቡት ሰዓት ካልተፈፀመላቸው በቁጣና በብስጭት ራሳቸውን የሚጎዱ ፣ያሹት ጉዳይ በወደዱ ጊዜ ካልተተገበረ ራሳቸውን በተስፋ መቁረጥ አርጩሜ የሚገርፉ ሰዎች እንዳሉ ለማሳየት ነው፤ነገር ግን ይህ ባህርይ አጓጉል በመሆኑ እያንዳንዷን የሰከንድ ሽርፍራፊ በትዕግስት የተሞላ ህይወት መምራት እንዳለብን መምከር የፈለገ ይመስላል፡፡

3.2 ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ግጥሞች

በዚህ ዐብይ ርዕስ የምንመለከታቸው የግጥም ይዘቶች የሚዳስሷቸው ጉደዬች ስለቅንጅት ፓርቲ፣ስለህዝብና ፓርቲ፣ስለዲሞክራሲ፣ስለቱርክ፣ለሀገር ደንታ ስለሌላቸው ግለሰቦች ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ግጥም ‹‹አበባ አፈጀች›› የሚለው ግጥም ሲሆን የሚያመለክተው በግንቦት 1997 የተካሄደውን ምርጫ ነው፡፡

እነሆ ክረምት አለፈ
ዝናቡም መጥቶ ሄደ …››
አበቦች ኰሩ አጌጡ

አበቦት ውኩል ተደረጉት ለቅንጅት ፓርቲ መሆኑን የምንቀበለው ሐቅ እንደሆነ ከሰዕሉ መመልከት ይቻላል፡፡ ይህ ፓርቲ ከምርጫው ቀን በፊት ባደረገው ከፍተኛ ቀስቀሳ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ነበርና ይህም እንዲታበይ በሩን ከፈተበት፡፡ኩራቱና መታበዩ ሳይገታ እነደውም እያየለ እስከ ምርጫ ዋዜማ ድረስ በትዕይንት መስኮትና በህትመት ውጤቶች ኢትዮጵያ፣አንደ ኢትዮጵያ የሚል ስብከቱን ተያያዘው፡፡

በኩራት አበጡ
በዕብሪት ተለበጡ
‹‹እመጋቢት›› ድረስ ባረንጓዴ … ቢጫ… ቀይ…
ቀለማቶች በኩል ምስጢሩን ገለጡ፡፡

በዚህ መልክ ቀጥለው በግንቦት ምርጫ ወቅት ቅንጅት ከፍተኛ ድምፅ አገኙ፤ይሁን እንጂ ብዙም ሳይቆይና ህዝቡ ለቅንጅት ያለው ፍቅር ሳይጠግግ የፓርቲው እንቅስቃሴ ዶግ አመድ ሆነ፡፡

ሁልጊዜ ውብ ነገር
ዕጣው ይኸው ነው ወይ?
ሁልጊዜም ውብ ነበር
ዕድሜው አጭር ነው ወይ?

በአጠቃላይ ግጥም ያማረ ነገር ሁሉ ፈላጊና ተንኳሽ ይበዛዋልና እንደማይበረክት አስረግጧል፤በመሆኑም የቅንጅት ፓርቲ በዘጠና ሰባት ምርጫ ማለፉን ሲናፍቅ ተቃራኒ ውጤት ማስመዝገቡ ከህዝቡ ጉጉት አኳያ አሳዛኝ መሆኑን ይገልፃል፡፡

ቀጣዩ ግጥም ‹‹ሕዝብና ፓርቲ›› የሚለው ግጥም ነው፡፡ በዚህ ግጥም ለወሳ የተፈለገው ደግሞ ህዝብ ለሚሻው ጉዳይ ይደርስለትና ተገን ይሆንለት ዘንድ ራሱን መስዋዕት ያደርጋል ብሎ ልቡ የተደለደለበትን ፓርቲ ተመራርጦ ዋና እነዲያበጅ እምነት ቢጥልበት ፓርቲው ማድረግ አለመቻሉን ያመለክታል፡፡

ነገሠበት መሰል
ልግምና ለበጣ
አቃተው መረጣ
እርግፍ አርጐ እንዲተው
ጠጉር መሰንጠቁን
ስንደዶ መፍለጡን
ላበቱን ወቀጣ

ፓርቲው ለህዝብ መልካም ሥራን ለመፈፀም ከመታተር ይልቅ በተቃራኒው አንዱ ፓርቲ የሌላውን፣ሌላው የአንዱን አላማ በማብጠልጠል መወራረፍን ተያያዘው፡፡

ወተቱ ተገፍቶ ቅቤው እንዲወጣ
ከእንግዲህስ ይብቃ
ይነገረው ባዋጅ
ሐቁ ይፋ ይውጣ
ሕዝቡ የሚወደውን …
ወይም የሚሻውን ወኪል ፓርቲ ካጣ፤
ምንችግር አለበት?
(ሚናው) ድርሻው ይቀያየር …
ፓርቲው ሌላ ሕዝብን
ፈልጐ ይምረጣ
(ሕዝብና ፓርቲ፣4)

ስለሆነም ስህተቱን ድክመቱ ሊነገረውና ሊገለፅ ይገባዋል፡፡ ለአሸናፊነቱ እንደቅራላ ሲለፋለት የነበረውን ህዝብ መታደግ ካልቻለ ሕዝቡ አይንህ ላፈር ይለዋል ይህ እንዳይሆን ግን ተቀባይነትን ሊያገኝ የሚያስችለውን መንገድ መቀየስ አለበት በማለት የተለያዩ ፓርቲዎች በምርጫ ዘጠና ሰባት ኢህዲግን ለመጣል የወጠኑት መንገድ አዋጪ ያልሆነው በራሳቸው ዝርክርክነትና ጠባብነት እንደነበር ለማሳየት የፈለገ ይመስላል፡፡ በአጠቃላይ በየፓርቲው የተሰገሰጉ አባላት የራሳቸውን ጥቅም ለመስጠበቅ እንጂ ለመህበረሰቡ አንዳች  ፋይዳ ለመበርከት እንዳልሆነ በመሆኑም ህዝቡ በፓርቲዎች እርካታ እንደሌለው ያጠይቃል፡፡

ሌለው ወፌ ‹‹ቆመችና ዶሮማታ›› የሚለው ግጥም ዲሞክራሲ በቃል እነጂ በተግባር ለማስፍን የተራራን ያህል የገዘፈ ችግር መጋፈጥ የግድ መሆኑን ፣ይህም ቢደረግ ላይከፋን እንደሚችልም ያሳያል፡፡

ቢያቅትህ ቢጎፈንንህም
ቢያሸርህ ትካሳለህ
ህመምክን ትድናለህ
ሽልማቱን ዶሮ ትኰመኩማለህ

ድሮ ድሮ ኰሶ የሚባል መድሃኒት ሲጠጣ መድሃኒቱን የሚወስደው ሰው ምሬቱንእንዳያስተውሰው እናቶች ተሰብስበው ‹‹ዶሮ ማታ ዶሮ ማታ›› ይላሉ ይህም ማለት አሁን ይህን ኮሶ ከጠጣህ ማታዶሮ ይታረድልሃል፡፡ ምክንያቱም መድሃኒቱን ማሻሪያ ዶሮ ስለሆነ እንደሽልማት ይበረከትልሃል ይባላል፡፡ ነገር ግን ላይሰጠውም ይችላል፡፡

ያን ማዶ ተረተር እንድናልፍ
ዲሞክራሲው እንዳይጨናገፍ
በወፌ ቆመች ብልሃት እንስለፍ
በዶሮ ማታ ብልሃት እንተቃቀፍ
(ወፌቆመችና ዶሮማታ፣12)

ልክ እንደዚህ ሁሉ ዲሞክራሲም በሀደር ላይ ከሰፈነ ፋይዳው ይህ ነው አይባልም ፣ ይሁን እንጂ ዲሞክራሲን ማውራት እንጂ መተግበር አዳጋች በመሆኑ ላይገኝ ይችላልና በተጨባጭ እስኪታይ በተስፋ መጠበቅም ታለቅ ጉብዝና ነው፡፡ በማለት ይናገራል በጠቅላላው የሀገራችን ዲሞክራሲ በቃል እንጂ በተግባር የለመም የሚሉ አንዳንድ ሰዎችን ሀሳብ የሚጋራ ይመስላል፡፡

ቀጥሎ "ብልሃት" የሚለው ግጥም በሀገራችን ግጭቶች ሲፈጠሩ አንድም መልካም በሆነ መንገድ አንድም የአንዱን ቀና ሀሳብ በሌላው ገልብጦ በመንገርና ነደሩ እንዲጋጋል በማድረግ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

በኔ አገር፤
ግጭትና ችግር
እንደ እሳት አደጋ
… ድንገት ነው ሚፈጠር፡፡
እሳቱ የሚጠፋው
ነገሩም 'የሚበርደው
በሁለት ብልሃት ነው፡፡
አንደኛው…
ምራቅ፣ ጨኸት ፣ አፈር፣ ውሃ በማራጨት
ሌላው … ነዳጅና በንዚል ጋዝ ሲለቀቅበት፡፡
(ብልሃት፣18)

በሁለቱ ስልቶች ስር በርካታ ንዑሳን መንገዶች እንዳሉ የሚያመለክተን አስር የተለያዩ ምስሎች የታተሙባቸው እጆች ይታያሉ፡፡ እነርሱም ስንፈርጃቸው በመልካም አካሄድ ውስጥ ‹‹ ኮስብ›› በሀይማኖታዊ ስርዓት(የሙስሊሞች ) ‹‹የሚቀሰቅሰው›› በእግዚአታ ፣‹‹አበባ››፣በፍቅር በመግዛት ‹‹አካፋና ዶማ›› አምራች ዜጋ በመሆን ለጥል ቦጣ ባለመስጠት ሲሆን በክፉ ስልት ስር ደግሞ ‹‹ብር›› በገንዘብ በመደለል ‹‹አፅም›› ነገር ግን በማውጣት በማውረድ ፣‹‹እባብ››፣ በመሰሪነት ሠላማዊ መስሎ ውስጥ ውስጡን በመጉዳት ፣‹‹የተጠላለፈ መስመር ›› ፣ነገሮችን በማያያዝ /የአንዱን ስለአንዱ / በጠቅላላው ሁለት ስልቶች አሉ ይበል እንጂ ወጣምወረደ በተለያዩ መንገዶች እንደምንጠቀም ይናገራል፡፡

ተከታዩ ደግሞ ‹‹አገር ለማን ነው›› የሚለው ግጥም ለሀገር ፍቅር ስሜት ደንታ የሌላቸውን ሰዎች በምፀት ሲተች ይስተዋላል፡፡

አገር ለድሀ ነው
መሄጃ ለሌለው
መሸጥ ለማይችለው

እነዚህን ባለስልጣናት ለኪሳቸው መደለብ እነጂ ስለህዝብ ጥቅም ግድ አይሰጣቸውምና ገጣሚውም ሀገር ችጋር አላምጦ ለተፋው ምናምንቴ ደሀ እንጂ ለአንተ

ምቾት መድረሻ ላሳጣህ ሀብታም ምንም አትሰርልህምና ሽቅጣት እያለ በምፀት ይተቻቸዋል፡፡

ድኃ ሆኖ በድርቅ ሥሚ ከሚጠራ
ቀውረሃት ወዲያው በገንዘቡ ኩራ

ከድህነት ወለል በታች ሆኖ ለምትዋዥቅ ሀገር ምንም ርህራሄ አያስፈለጋትም ‹‹ትንሽ ሰው ትንሽ ነው›› እንዲባል ከምስኪን ሀገር አንዲት አታገኝም ውድቀት እንጂ በማለት ስግብግቦችን ፣ለሆዳቸው ያደሩ ሰዎችን /ባለስልጣኖችን አጥብቆ ይሳለቅባቸዋል፡፡

በመቀጠል ‹‹ቱርክ›› በሚል ርዕስ የቀረበው ግጥም ይዘት ቱርኮች ኢትዮጵያን በጦርነት ባያሸንፉትም ባትሌቲክሱ መርታታቸው ግን የላቀ ደስታን እንዳጎናፀፋቸው ያመለክታል፡፡

በአባ ታጠቅ ዘመን
በአባ በዝብዝ ዘመን
ድል ያደረግናቸው
ደጋግመን በመውቃት ያበራየናቸው

ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ጀምሮ ‹‹ ቦሬሳው ካሳ ከቱርክ ይዋጋል እንኳን ከአንካሳ›› እየተባለ ይዘፈን ነበርና በዘፈንም ብቻ ሳይሆን በጀግንነታችን ቱርኮች ድንበራችንን እንዳይነኩ አድርገን እንደነበር ይገልፃል፡፡

መቶ ሀለት መቶ ዓመት
በሽሽግ አድፍጠው
ቢመጡ አድብተው
በኃይሌ ደራርቱ ደጋግመን ወቃናቸው

እንደገናም ከሁለት መቶ ዓመት በኃላ በአትሌቲክሱ ዘርፍ ሊገዳደሩን ሲመጡ በውድ አትሌቶችን አላሽቅናቸው፡፡

ቂም ያልያዘ መስለው በሰላሙ ዘመን
በገንዘብ ገዛና በድህነታችን
መላ ዘየዱና ፣በራሳችን ዘፈን
እንዲህ ዘመሩልን …
በገዛ ልጃቸው አርባገረፍናቸው፡፡
(ቱርክ፣100)

የሞከሯቸው መንገዶች ሁሉ አላዋጣ ሲላቸው አማራጫቸውን የበታችነታችንን መጠቀም አድረገው በዝቅተኝነታችን ተገን አትሌት ኤላፐን አብይ ለገሰን ከመዳፋችን በመንጠቅ በገዛ አኮርባጃችን የለጠለጡንን ያልጠገገ ቁስል በሬዛቸው አጅበው ጓጉጡን በማለት ቁጭቱን ይገልፃል፡፧

የሚቀጥለው ‹‹እችክችክ ሁለት›› ሀገራችን ኢትዮጵያ እኛ ልጆች ከድህነት እንድንታደጋት ብትማፀነንም አቅም ስለሌለን ግን ምንም መፈየድ እንዳልቻልን ያስተዛል፡፡

በእችክአችክ መዝሙር
ተቃኝቶ ዜማችን

በብካይና ራሮት ታጅበን ፣በድህነት ገመድ ተጠፍንገን ለዘመናት ኖረናል ፡፡ አሁንም ቢሆን የኑሮ ውድነት ቅምስቅላችንን እያሳየን ዘወትር እዬዬ ያስብለናል፡፡

ሀብቱን እኩል በማያካፍል
እናድህነቱን እኩል እንካፈል
በሚሉ ባዶ ሆዶች ፣በኔና አንቺ መሀል
ምንልዩነት ኖሮ - ሙግት ይገጠሟል
ቃል ኪዳን ይጋቧል
ምናችንን ልንካፈል
በልቦና አልቦ መሀል

(እችክችክ ሁለት-71)

ይሁን እንጂ በሰቀቀን ከምንኖረው ከእኛ ሀገራችን አያሌ ትሻለች፡፡ ባለን አቅም እንድንቤዣሞግተናለች፡፡ ነገር ግን የድህነት ግጥም ተገጥሞለት ፣የድህነት ዜማ ወጥቶለት ሠርክ ድህነት በሚዘመርላት ሀገር ውስጥ መኖር ወደ አዘቅት ህይወት ስቶ እንደመግባት መሆኑ ይታመናል ፡፡ በመሆኑም ኢምንት ለሌለው ምኪን ኦና በሆነች ኢትዬጵያ ውስጥ መኖር ኪሳራ እንጂ ትረፍ የለውም በማለት ይናገራል፡፡ የግጥሙ ጠቅላላ ሀሳብ ኢትዬጵያ ውስጥ በኖር እድሜ ዘመንን በኑሮ ንረት ቀመሳቀል ውጪ እኛም ለሀገራችን ሀገራችንም ለእኛ ‹‹እከከኝ ልከክህ›› ፣ድህነትን ማራገፍ ይሻላል የሚል አንድምታ አለው፡፡

3.3 ሀገራዊ ጉዳዮችን የሚቃኙ

አለቱን እንደፈለሱት ጠብታዎች
ዘብጡን እንደሸረሸሩት ጎርፍ ጎርፎች
ምድሩን እንዳነጡት የክረምት ዝናሞች
ድንጋዮቹን እንደፋቃቸው ውሃ
ጥሉሉን ከበተሃ
አየቀላቀልን
ዕውነት ነው እያልን
በየጉባኤው ስንማማል
ስንታመም ስናስታምም
ጊዜው ደረሰና እንዴት እንደማንም
መቶዋን ተማምነን ሳንፈራረም
ገስግሳ ደረሰች እመት ሚሊኒየም፡፡
((2ሺ.ህ) የምስራች! ፣18)

በግጥሙ ወሬና ውሀን በማነፃፀር፣ ጎርፍ በምድር የሰከነውን ነገር ሁሉ እየበጠበጠ እንደሚጥረገረግ ሁሉ እኛም እውነቱንም ሀሰቱንም ስንቀባጥርና ሰላማዊ ነገር ላይ ሽብርን ስንዘራ ሚሊኒየምን መቀላቀላችንን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም ‹‹መቶዋን ተማምነን ስንፈራረም›› ሲል አንዳንድ ሰዎች ኢትዮጵያ ሀገራችን የመቶ አመት በለታሪክ እንጂ ሁለት ሺህ አመት አላስቆጠረችም በማለት አሁን ድረስ ሚሊኒየምን እንዳልተቀበልን የሚከራከሩ ሰዎች መኖራቸውን ለመግለፅ ነው፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ ፓርቲ ስለራሱ ድርጅት አላማ ፅኑነትና ሀቀኝነት ብቻ ሲደሰኩር ስናስበው ሚሊኒየምን እንደተቀበልናት ይጠቁማል፡፡

ዜጋዬ እመቤቴ! ለሁለም የሚፈርድ
የእኩል ዳኛ እስኪገኝ
ሁሉን እኩል የሚያዝ

ህዝቡን ለመክር ምንም ያህል እንካ ተቆርቆሪ አስተዳደር ባታገኝ ፣ሀገርንና ገንን ለመበጥበጥ አሰስገሰስ ወሬዎችን የሚቀባጥሩልህን አእምሮህም ሆነ ልቦናህ አንጥሮ ይመልሰው እንጂ አትቀበላቸው፡፡ በሁለት ሺህ ያደረስህም የጋራ ፈረስ አለመሆን ነውና በርታ በማለት ያጠናክራል፡፡

ሌላው ‹‹ረታ›› ነው ይህ ግጥም ኢትዬጵያ አንድም ከጥንት ጀምሮ ነፃነቷን አስጠብቃ የኖረችመሆኗን ሲያመለክት አንድም ከድህነት ሳትላቀቅና ለውጥ ሳታሳይ ለሁለት ሺህ መድረሷን ያመላክታል፡፡

ጦብያ- እንደለመደች
ይኸው- ዛሬም ረታች
2ሺ.ህ ለአልቦ ያው ድል አደረገች

ወይም አሸነፈች
ወይንም አቸነፈች
አጠመንጃ ይልቅ - ታሪክና ትዕግስት
ይልቀሉ እያለች
ኢትዮጵያ ዛሠም ረታች፡፡

ሀገራችን ትዕግስትን ስንቅ በማድረግና መቻቻል የስፈነበት ህይወት በመምራት ታሪኳን አሰጠብቃ ለሚሊሊየም መድረሷ እንደድል አድራጊ ያስቆጥራታል ሲል በሌላ መልኩ ደግሞ አፈሪካ በግሎባላይዜሽን ሂደት በዝረራ የወጣች አህጉር እንደሆነች ይናገራል፡፡ በዚህም ኢትዮጵያ በአፍሪካ እንደመገኘቷ መጠን የአፍሪካ መሸነፍ ለኢትዩጵያም ሽንፈቷ ነው፡፡ ስለሆነም ሌለው ሰልጥኖ ጨረቃ ላይ በከተመበት ዘመን ኢትዮጵያ ግን የግሎባላይዜሽን ጥሩ ተፎካካሪ ሳትሆን ‹‹ታሪክ›› የሚለው ቃል ዘወትር አባቶቻችን እንዲህ አደረጉ በማለት ‹‹ትዕግስት›› ዝምታን ተረጋግቶ መቀመጥን ፣‹‹ጠመንጃ›› የድህነት ማጥፊያ መሣሪያን ይወክላል፡፡ ስለሆነም ድህነትን ለማጥፋት ከመትጋት ይልቅ ያለምንም ጥረት መቀመጧ በባዶው ለሚሊኒየም እንድትደርስ አድርጓታል ለማለት የፈለገ ይመስላል፡፡

ቀጥሎ ‹‹እመነትና ፍቅር›› በሚለው ግጥም የሀደሩ አለመበልፀግ እጅግ ያስደመመውና ልቡ የተነካ ሰው ተስሏል፡፡

ከለመዱት ገላ ፣ከሚወዱት ጋራ
እምነት ፍቅር ካለ፣ይገፋል ተራራ፡፡
ታዲያ ጦቢያ ሀገሬ …
እምነት አጥታ ነው ወይ?
ፍቅር አጥታ ነው ወይ? ከእምነትም እምነት
ተራራ እንኳን ቢቀር
ጠጠርፈቅ ማድረግ
መግፋቱ ያቃታት፡፡

‹‹እምትፈቀር ካለ ይገፋል ተራራ›› ሲባል የምሰማው እውነት ከሆነ ሀገሬ ህልቆ መሳፍረት እምነትና ፍቅር ተጎናፅፋ ለምን ማደግ አቃታት? እንኳንስ ከፍ ብላ መታየት ይቅርና ድህነትን መርታት የተሳናት ለምን ይሆን? በማለት ጥያቄውን ያቀርባል፡፡ በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ካደጉት ሀገራት ጎራ አለመመደቧ አስገራሚ መሆኑን ለመጠቆም ሽቷል፡፡

### 3.4 ሌላ

በዚህ ዋና ርዕስ ስር የሚተነተነው ‹‹በትረ-አሮን›› ግጥሙ የጌታችን የአምላካችንና መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እናት ማርያምን ያወድሳል፡፡

እንዴታ አንቺን ስጠኝ
ምን ያህል ቢወደኝ

ለዚህ ዓለም ወረት ግድ የሌለሽ ማርም ምንብዬ ላወድስሽ፡፡ አምላክ አንቺን ስለሰጠኝ እጅግ እንደሚወደኝ አመንኩ፡፡

የተመረዙ ሁሉ
ወዳንቺ ስላዩ ፈውስን ያገኛሉ፤
እንኳንስ አንቺንና
ጥላሽን የተደባበሱ
ድነው -ያድናሉ

በእርሷ ያመኑ ሁሉ በድህነት መርከብ እንደሚገባ ይወቅ፡፡ ለየዋሀን ስጦታቸው ለእርጉማን ግን አላመኑ ካቻምና አንቺን የመሰለ እናት ያጣሉ ይህም የቅታቶች ሁሉ ቅጣት ነው፡፡ አንቺ የሙሴ ፅላት ፣የአሮን በትር የሆንሽ እመቤቴ ለሁሉም ፍጥረት መንገድ መሪነሽ ለማለት ‹‹አቅጣጫ አመልካች ፋና ትሆኛለሽ፡፡›› በሚለው ስንኝ ይገልፃል፡፡ በአጠቃላይ አምላክ ወዶኛልና አርምሞ ትፅግስትሽ የበዛ እናቴ አንቺን መሳይ እናት ላገሰኝ አምላክ ምስጋና ይድረሰው በማለት ያወድሰዋል፡፡

## ማጠቃለያ

ጥናቱ  በአቶ አብርሃ ረታ እችክችክ የግጥም መፅሀፍ ውስጥ የወጡ ግጥሞችን ተመልክቷል፡፡ ግጥሞቹ በሚያነሳቸው ርዕስ ጉዳዮች ተመድበውና ይዘታቸውም ተተንትኖ የሚያነሱትን ጉዳይ ለመቃኘት ተጭሏል በርዕሰ ጉዳያቸው ስንመድባቸውም አብዛኞቹ መህበራዊ ሂስን የሚሰጡ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በተጨማሪም ስለፖለቲካና ሀገር ጉዳዮች የሚንፀባረቁባቸው ግጥሞችም በጥናቱ ተዳሰዋል፡፡ በዚህም የግጥሞቹ ይዘት ሲተነተን የያዙት ዋና ዋና ሀሳብ ምን እንደሆነ ለመየት ተችሏል፡፡

በግጥሞቹም እንደሌሎቹ የስነ-ፅሁፍ ዘሮች ሁሉ የማህበረሰብን ጠንካራና ደካማ ጐን ፣የማህበረሰቡን መሻት አመለካከት ፣የፍቅር ህይወት የሀገሪቱን ፖለቲካ ስርዓት እነደ አርአያ ምርጫ 97 የፓርቲዎች ሂደት ፣ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲሁም መንፈሳዊ ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የግጥሞቹን ጥልቀትና አመራማሪነት ሲቃኝ አብዛኞቹ በቃላት መረጣቸውና በሀሳባቸው ጥልቅነትና ጥቅልነት ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ሲሆን የሚሰጣቸው ርዕስ ጉዳዮችም ወቅታዊና አንገብጋቢ ፣የመህበረሰቡን ውስጣዊ ስሜት ያዳመጡ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ግጥሞቹ ገጣሚው ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሀሳብና ስሜት የማስተላለፍ አቅማቸው የላቀ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

# ዋቢ-መፃሕፍት


ብርሃኑ ገበየሁ፡፡ የአማረኛ ስነ-ግጥም፡፡ አዲስ አበባ ፣ አልፋ አሳታሚዎች፣1999 ዓ.ም

ዘሪሁን አስፋው፡፡ የሥነ-ፅሁፍ መሠረታውያን፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1998 ዓ.ም

ደረጀ ገብሬ፡፡1995፡፡ "በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በዲፕሎማው መርሃ ግብር የሚሰጡ አብይ ኮርሶች ይዘት ትንተና" አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ጥናት

አዲስ አድማስ ጋዜጣ፡፡ አዲስ አበባ፣ ቅፅ 9 ቁጥር 486 ፣ ግንቦት 15፡2001፡፡

Burton in and CJH checks filed .African poetry in English and introduction to practical criticism. London: the Macmillan press to, 1979.

Academic American Encyclopedia, USA; Gorlia inc.vol.15,1986.

Http... www./ake/ and schools org/edtec/inspection/poetr.htm/.

## ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1. The word of a poem... may achieve or unique meaning that is almost independent of their dictionary sense and peculiar to the work in which they are used.

2. Poetry analysis is the process of investigating poem's from, content and history in an informed way , with the aim of heightening one's own and others understanding and appreciation of the work.

3. Meaning includes sentiments and emotion as well as ideas; an important part of the meaning of a poem is what it makes a reader feel.